

☙35-1❧

# ከስርቆት ጠባይ እንሸሽ

ከብዙ ዓመት በፊት አንዲት የሂንዱ እምነት ተከታይ የነበረች ሴት፥ የእግዚአብሔርን ቃል በማንበብ ብቻ ወደ ክርስትና መጣች። ባሏ እንደ እርሷ አማኝ ስላልነበረ፥ በእርሱ በኩል ብዙ ችግርና ስደት ይደርስባት ነበር። ይህንን የተገነዘብ አንድ ሚሲዮናዊ አንድ ቀን "ባልሽ በኃይል ሲናደድና ሲቆጣሽ እንዲሁም ሲያሰቃይሽ ምንድነው የምታደርጊው?" ሲል ጠየቃት። ሴትየዋም ስትመልስ፥ "ምግቡ አይጣፍጥም ያለ እንደ ሆነ፥ የበለጠ ጥሩ አድርጌ እሠራለታለሁ፤ ቤቱ አልተጠረገም ቢል፥ የበለጠ ጥሩ አድርጌ እጠርጋለሁ፤ ክፉ ቃል ሲናገረኝ፥ ደግ በመናገር ቁጣውን አበርዳለሁ። በአጠቃላይ ክርስቲያን ከሆንኩ በኋላ የተሻልኩ ሚስት የተሻልኩ እናት መሆኔን እንዲያይ ዕድል እሰጠዋለሁ" ስትል መለሰችለት። ያ ሰው ሚሲዮናውያን የሚሰብኩለት ስብከት ባይጥመውና መቀበል ቢያቅተውም፥ ሚስቱ በየቀኑ በሕይወቷ የምትሰብክለትን ስብከት እምቢ ማለት ስላልቻለ በመጨረሻ ልቡን ለጌታ አስረከበ።

ዓለማውያን ቤተ ክርስቲያን ስለማይመጡ ወንጌል ሲሰበክ አይሰሙም። ጥሬ ቃሉ ቢሰበክላቸውም መቀበላቸውን እንጠራጠራለን። ክርስትና የሃይማኖት ሥርዓት እንጂ እውነትም በሰው ሕይወት የሚታይ የሕይወት ለውጥ ያለበት አዲስ ልምምድ መሆኑን አያውቁም። በዚህም ምክንያት በዘለዓለም ፍርድ ውስጥ እየኖሩ ናቸው። እኛ ጌታን የምናውቅ ሰዎች የእነዚህ ሰዎች መጥፋት ግድ ይለናል፤ ያሳስበናል። እንዲሁም ኃላፊነትና ተጠሪነት አለብን። ስለሆነም፥ እያንዳንዳችን በአካባቢያችን ላሉት ላልዳኑት ሰዎች የደህንነትን ወንጌል መስበክ ኃላፊነትና ግዴታ አለብን።

ምናልባት ብዙዎቻችን ጥሩ ሰባኪዎች ስላልሆንን ቃሉን ገላልጠን ልናስረዳቸው አንችልም ይሆናል። ይህ በመሆኑ ካለብን ኃላፊነት ማምለጥ አንችልም። ኤም ባሉ የተባለ ጸሀፊ "ስብከት በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፤ በህይወት ልምምድ ማሳየት ግን ከስብከት ይበጣል። ተጠራጣሪን በክርክር ከመመለስ ይልቅ የተቀደሰ ሕይወት ኖሮ በማሳየት ማሳመን ይቀላል" አለ። ሁላችንም በሕይወታችን ምስክሮች መሆን እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦ ማንበብ ባይችሉ የእኛን ሕይወት በየዕለቱ ማየት ይችላሉ። ከላይ ታሪኳን የሰማናት ሴት፥ ለባሏ የሰበከችለት በሕይወቷ ምስክርነት እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን ገልጣ አስተምራው አይደለም። የእኛስ ሕይወት በሌሎች ሰዎች ሲታይ ምን ይመስላል? ሴኔካ የተባለው ጸሐፊ "ሰዎች በጆሮአቸው ከሚሰሙት ነገር ይልቅ በዓይናቸው የሚያዩትን ማመን ይቀላቸዋል" አለ። መጽሀፍ ቅዱስ እኛን አማኞችን "ነገር ግን የጠራችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተም በኑሮአችን ቅዱሳን ሁሉ" ሲል ይመክረናል (1ጴጥ. 1፥15)።

ዓለማውያኖች ሕይወታችንን ልብ ብለው ተመልክተው "እርሱስ ከእኔ የተሻለ አይደለም፤ እሰርቃለሁ፣ እርሱም ይሰርቃል፣ እዋሻለሁ፤ እርሱም ይዋሻል" በማለት ክርስትናን እንዳይገፉብን እኔና እናንተ ሕይወታችንን በጥንቃቄ መምራት ያስፈልገናል። "ከስርቆት እንሸሽ" የሚለውን አርዕስት ከላይ ስትመልከቱ፥ "እኔ ክርስቲያን ስለሆንኩ፥ አልሰርቅምና ትምህርቱ አይመለከተኝም" ማለታችሁ አይቀርም። የእግዚአብሔር ቃል ውስጣችን ገብቶ አቋማችንን ስለሚያሳየን ከታገስን ስንቶቻችን እንደምንሰርቅ ለመረዳት ብዙ ጊዜ አይፈጅብንም። የሚያሳዝነው ግን የብዙዎቻችን ህሊና ፍጹም የደነዘዘ በመሆኑ ኃጢአታችን ላይሰማን ይችላል። "ህሊናዬ ንጹህ ነው፤ ኃጢአት የለብኝም ማለት የሚችል ሰው ይኖራልን?" (ምሳሌ 20፥9)። በሥርቆት ልምምድ ውስጥ ብዙ ዘመን ስለ አሳለፍን አንዳንዶቻችን ፈጽሞ አይሰማንም። ኤች ሲ ትሩምቡል የተባለው ሰው "ሕሊና ለሰው የተሰጠው ወደ ትክክለኛነት እንዲመራው ሳይሆን፥ ትክክል ካልሆነው ነገር ይልቅ ትክክል የሆነውን ነገር እንዲመርጥ እንዲያደፋፍር ነው። ሕሊና

ሰውን ትክክል ያልሆነውን ትቶ ትክክል የሆነውን እንዲያደርግ ይነግረዋል እንጂ፥ ትክክል የሆነውን እንዲያደርግ አያስገድደውም። ሰው ግን የራሱን ውሳኔ አድርጎ ትክክለኛው ይሄ ነው በማለት በዚያ ላይ ሕሊናውን ካሳረፈና ካለማመደ፥ ያ ሰው ፍጹም የጠፋና ተስፋ ቢስ ነው። እያወቀ ወይንም ሆን ብሎ ሰይጣንን ማገልገል ከጀመረ ያ ሰው በጥፋት ዓለም እርቆ ሄዷል" አለ። ስርቆታችንንና ከመስመር የወጣውን ድርጊታችንን "ልክ ነው" ብለን በመቀበል እራሳችንንም ሆነ ሌሎችን የምናሳምንበት ወይንም የምንከራከርበት የመውጫ ቀዳዳ ማዘጋጀቱ ከበደለኛነት ስሜት ነጻ አያደርገንም።

### የዕቃ ወይንም የገንዘብ ስርቆት

በዓለም ውስጥ ከፍተኛ ስርቆት ይካሄዳል። ሠራተኞች ከአሠሪዎቻቸው ብዙ ገንዘብ ይሠርቃሉ። በአሜሪካን አገር ውስጥ የበላይ ባለሥልጣናት በዓመት 40 ቢሊዮን ብር ከመንግሥትና ከግል መሥሪያ ቤት ይሠርቃሉ። ይኼም በየመንገዱ ከሚደረገው ቅሚያና ዝርፊያ በአሥር እጅ እንደሚበልጥ ተረጋግጧል። በተራ ሠራተኞችም ብዙ ይሠረቃል። ለምሳሌ ያህል "ቼን ድራግ ስቶር" (Chain Drug Store) ከጠቅላላ ሽያጭ ላይ አራት ከመቶ (4%) ከምግብ ኢንዱስትሪ ደግሞ ከጠቅላላ ሽያጭ ከመቶ ሦስት (3%) በተራ ሠረተኞች ይሠረቃል ይሄም ሲተመን ብዙ ሚሊዮን ብር እንደሚሆን ታውቋል። የሌላውን ድካምና ውድቀት ማውራት በጣም ይቀላል። ለመሆኑ እኛ እራሳችንን "አማኝ" ብለን የምንጠራው ክርስቲያኖችስ ምን ዓይነት ይዞታ ይኖረን ይሆን? ተጋልጦ የሚታየው የዓለማውያን ሕይወት ብቻ ሳይሆን የእኛም ሕይወት በግልጽ ይታያል። ስለዚህም ከዚህ ዓይነቱ ነቀፋ ፍጹም ንጹሆች አይደለንም። የእግዚአብሔር ቃል ግን "የዚህን ዓለም ሰዎች ክፉ ጠባይ አትከተሉ" (ሮሜ 12፥2) ሲል ይመክረናል።

መስረቅ የተከለከለ እንደሆነ መጽሀፍ ቅዱስ ይናገራል። "አትስረቅ" (ዘጸ 20፥15)። "ሌባ ሁሉ ከምድር ይወገዳል" ይላል (ዘካርያስ 5፥3)። በአዲስ ኪዳንም ኢየሱስ "አትስረቅ" (ማቴ 19፥18) ሲል አስተምሮአል። ሃዋርያው ጳውሎስም "ይሰርቅ የነበረ ከእንግዲህ ወዲያ አይስረቅ፥ ይልቅስ ለችግሮኞች የሚያካፍለው ገንዘብ እንዲኖረው በገዛ እጆቹ መልካም ነገርን ይሥራ" (ኤፌ 4፥28) ሲል አስተምሮአል። የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ "አትስረቁ" ቢልም በብሉይ ኪዳንም ዘመን ሆነ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሰዎች በተለያየ ጊዜ ሲሰርቁ ይገኛሉ። አካን ካባና ምዝምዝ ወርቅ ሰረቀ። "ካገኘነው ዕቃ መካከል ውብ የሆነ የባቢሎናውያን ካባ ሁለት ኪሎ ያህል የሚመዝን ብርና ግማሽ ኪሎ ያህል የሚመዝን ምዝምዝ ወርቅ አየሁ፤ እርሱንም ለማግኘት ብርቱ ፍላጎት ስላደረብኝ ወስጃቸዋለሁ፤ እነርሱንም ብሩ ከታች ሆኖ በድንኳኔ ውስጥ ተቀብረው ታገኛቸዋለህ" አለ (መጽሐፈ ኢያሱ 7፥12)። በአካን ሥርቆት ምክንያት የእሥራኤል ሕዝብ ተቀጣ። የመጀመሪያው የእሥራኤል ንጉሥ የነበረውም ሳኦል ከምርኮ ያገኘውን ማጥፋት ሲገባው ደብቆ ለራሱ እንዳስቀርና ያን እግዚአብሔርን እንዳስቆጣው እናነባለን።

በእኛስ ዘመን ክርስቲያኖች ሆነን እንሰርቅ ይሆን? የራስችን ያለሆነውን እንድንወስድ ያልተፈቀደልንን በድብቅ እንወስድ ይሆን? እርግጥ ነው ብዙዎቻችን የኑሮ ጥበት አለብን። በተለይ በውጪ አገር ከገቢው ይልቅ ወጪው ብዙ ነው። በዚህ ምክንያት ክርስቲያኖች የራሳቸው ያልሆነውን ለመውሰድ ወይንም ለመስረቅ ብዙ ፈተና አለባቸው። ገንዘብ ተቀባይ፣ የዕቃ ግምጃ ቤት ሃላፊዎች፣ ገንዘብ ባንክ አስገቢና አስወጪዎች ሆነው የሚሠሩ ክርስትያኖች አሉ። ብዙ ብር ልዩ ልዩ ዕቃዎች በእጃቸው ውስጥ እምነት ተጥሎባቸው ያልፋል። ከዚያ ውስጥ ጥቂት ቢወስዱ አይታወቅም ይሆናል። ያለባቸውን የኑሮ ጥበት ሲመለከቱ ያኔ ፈተናው የበለጠ ይሆናል። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቃል "በማጭበርበር ትርፍ ለማግኘት ብትሞክር ቤተሰብህን በችግር ላይ ትጥላለህ" (ምሳሌ 15፥27) ሲል ያስጠነቅቀናል።

ሰይጣን ዝም ብሎ አይመለከታቸውም። "በአዕምሮአችሁ ተጠቀሙ" በማለት ያደፋፍራቸዋል። ልዩ ልዩ ምክንያት ይሰጣቸዋል። ከምክንያቶቹ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ 1) ብዙ የምትከፍለው ዕዳ አለብህ 2) የምትወስደው ነገር አስፈላጊ ለሆነ ነገር እስከ ሆነ ድረስ ምንም አይደለም። ለታመሙ እናትህ መድኃኒት ከሱቁ ብትወስድ የታመመ ሰው እረዳህ እንጂ ሰርቀህ አይባልም። 3) አሠሪህ እኮ ያለአግባብ

ጉልበትህን እየበዘበዙህ ነው፤ ገንዘቡ የአሠሪህ ብቻ አይደለም፤ በአንተ ጉልበት የተገኘ በመሆኑ ብትወስድ ለራስህ ደሞዝ ከፈልክ እንጂ ሠርቅህ አይባልም። 4) ወደህ ችግርህን አቃልና ባይሆን ንስህ ትገባለህ። 5) ባይሆን አሥራትህን ከመቶ አሥር በመክፈል ፈንታ ከመቶ ሃያ ወይንም ሰላሳ ትከፍላለህ በማለት ከሠረቀው ገንዘብ ለእግዚአብሔር እንዲያካፍል ሰይጣን ሞኝ ነውና ሳይመክረው አይቀርም።

ከላይ የተዘርዘሩት ምክንያቶች ሁሉ ክርስትያን የራሱ ያልሆነውን ነገር እንዲሰርቅ ፍቃድ የሚሰጡ አይደሉም። በልክ ወይንም በአቅም ለመኖር እራሳችንን ማለማመድ እራስን ከፈተና መጠበቅ ይሆናል። ለፍላጎታችን ገደብ ወይንም ማሠሪያ ካልደረግንለት "በቃኝ' ማለትን አንችልበትም። "ብርን የሚወድ ብር አይቶ አይጠግም ሀብታም ለመሆን የሚፈልግም ሰው ትርፍ አግኝቶ አያልፍለትም ይህም ከንቱ ነው" ይላል (መክብብ 5፥10)። የስርቆትን ውጤት መጽሐፍ ቅዱስ ሲያስረዳ "ቀማኝነት የቀማኛው ሕይወት መጥፊያ ነው" ይላል (ምሳሌ 1፥19)። በስርቆት እራስን አሳድጎ ትልቅ ኑሮ መኖር በማያቋርጥ የህሊና ክስ ውስጥ መኖር ነው። "ሀብታም ሆኖ በሁከት ከመኖር ይልቅ ድሃ ሆኖ እግዚአብሔርን በማክበር መኖር ይሻላል" (ምሳሌ 15፥16) ይላል መጽሐፍ ቅዱስ።

በቤተ ክርስትያን ውስጥስ የሚያደርግ ስርቆት ይኖር ይሆን? በአሜሪካን ውስጥ በየጊዜው በጋዜጣና በሬዲዮ የምንሰማው ብዙ ነው። በእኛስ በኢትጵያውያኖች መካከል ይህ ችግር ይኖር ይሆን? የማይታየው እንደ ፈረንጆቹ ጉዳችንን የሚዘከዝክ ጎርጓሪ ጋዜጠኛ ስለሌለብን ይሆን? ይህ ፈተና እግዚአብሔርን ከሚወዱና ከሚያገለግሉ ሰዎችም የራቀ አይደለም። ብዙ ገንዘብ በቤተ ክርስትያን አካባቢ ይባክናል። በቀጥታም ባይሆን ሥርዓት በአጣ የገንዘብ አወጣጥ ምክንያት የእግዚአብሔር ገንዘብ ሊባክን ይችላል። ለምሳሌ 1) ለአንድ ዓይነት ፕሮጄክት ተብሎ ገንዘቡ ይሰበሰብና ያለሰጪዎች ፈቃድ ለሌላ ነገር ይውላል። 2) በገንዘቡ አካባቢ ለሚገኙ ሰዎች ልዩ ወጪ ተብሎ የሚባክነው ገንዘብ 3) በሁለት በኩል የሚያመርቱ አገልጋዮች (ከቤተ ክርስትያን ደሞዝ ይቀበላሉ፤ ከየግል ሰዎች ደግሞ ቤተ ክርስትያኒቱ ሳታውቅ የግል አሥራት ይሰበስባሉ። 4) የቤተ ክርስትያን መሪዎች ስብሰባ የሚያደርጉት ብዙ ገንዘብ የሚያስከፉሉ ሆቴሎች ወይንም መናፈሻ ቦታዎች ይሆናሉ። 5) በቤተ ክርስትያኒቱ ወይንም በድርጅቱ ገንዘብ እንግዶቻቸውን የሚያስተናግዱ ወይንም ወዳጅ የሚያፈሩበት ብዙዎች ናቸው።

ማንኛውም መንፈሳዊ መሪ በተለይ በገንዘብ አካባቢ የሚገኝ ሁሉ ከነቀፋ እራሱን ለመጠበቅ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል። ብዙ ጊዜ በተለይ በእኛ በኢትዮጵያውያን መካከል በሚፈጠረው ዝርክርክነት ብዙ ሃሜት እንዲሰማ ይሆናል። ለዚህ ሁሉ መድኃኒቱ ትክክለኛ የሂሳብ አሠራር፣ ትክክለኛ ቁጥጥር (ዓመታዊ ኦዲት) ማድረግና ውጤቱን በግልጽ ለሚመለከተው ሁሉ መስጠት አስፈላጊ ነው። ይህን ማድረጉ እራስን ከፈተና መጠበቁ ብቻ ሳይሆን፥ ብዙዎች ስለ ገንዘብ አያያዝና አወጣጥ የሚኖራቸውን ጥያቄ ይመልሳል።

..........................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**